# 7. አላይድ (Allied) የጤና አገልግሎቶች

ልዩ የሆነ የበሽታ ዓይነት ለማከም የሰለጠኑ ብዙ የጤና ባለሙያዎች አሉ። እነዚህ የ'allied health' ባለሙያዎች ተብለው ይጠራሉ አላይድ የጤና ፕሮፌሽናሎች በሆስፒታል፣ የሕክምና ማእከል፣ ክሊኒኮችና የግል የህክምና ማእከላት ይሰራሉ። አንዳንድ የሚሰጡት አገልግሎቶች በመዲኬር የሚከፈል ነው። ቀጠሮ ከመያዝዎ በፊት ጠይቀው ማረጋገጥ ጠቃሚ ነው። ብዙ የጤና ዋስትና ድርጅቶች ለአላይድ የጤና አገልግሎቶች የሚከፈል ወጪ ይሸፍናሉ።



## አውዲኦሎጂ (Audiology)

- አውዲኦሎጂስቶች የሚባሉ፡ የመስማት ችግር ወይም ተመሳሳይ የመረዳዳት ችግር፡ በመመርመር እንዲሁም እንዴት መከላከል እንደሚቻል በተመለከተ ጥናት ያደረጉ ናቸው
- በሕጻናቶች፣ በልጆች፣ እና አዋቂዎች፣ ላይ የመስማት ምርመራ በማድረግ፡ ሕክምና የሚሰጡ ናቸው
- አውዲኦሎጊስቶች በሆስፒታል፣ በኮሚኒቲ አገልግሎቶች እና እንዲሁም በግል ይሰራሉ። ለራስዎ ወይም ለልጅዎ የመስማት ችግር ካጋጠመ፡ ከቤተሰብዎ ሐኪም (GP) ወደ ስፔሻሊስት እንዲልክዎት ይጠይቁ
- የአውስትራልያ የአውዲኦሎጂካል ሕብረተሰብ (Audiological Society of Australia) www.audiology.asn.au



## የተመጣጠነ ምግብና የአመጋገብ ጥናት (Dietetics)

- ዳያትሪሻን የሚባሉ በሰዎችና በምግብ መካከል ያለው ግንኙነት የሚያጠኑ ሲሆኑ፡ ጤና የሚሰጥ የምግብ ምርጫ ያደርጋሉ
- ዳያትሪሻን የተመጣጠነ ምግብ የሚያጠኑ ሰዎች በህዝብ ሆስፒታሎች፣ የኮሚኒቲ የጤና ማእከሎች እና እንዲሁም በግል ይሰራሉ
- አንዳንድ አገልግሎቶች በ Enhanced Primary Care Program በታች ሆነው በመዲኬር ይከፈላሉ። ይህን በተመለከተ የቤተሰብ ሓኪምዎን (GP) ይጠይቁ
- ዳያትሪሻን ማህበር በአውስትራልያ በዚህ ዌብሳይት ይመለከቱ www.daa.asn.au



## ኦኩፔሽናል (Occupational) ቴራፒ

- ኦኩፔሺናል ቴራፒስት ሰዎች የእለተ ኑራቸው ለመምራት ያግዛቸዋል። በበሽታ፣ የአካል ጉድለት ወይም አደጋ ምክንያት አንዳንድ ሰዎች አንዳንድ ነገሮች ለማድረግ ይቸገራሉ
- ኦኩፔሺናል ቴራፒስት አዲስ የአሰራር ቴክኒክ ያስተምራሉ፣ ሰዎች በራሳቸው ድርጊታቸው ለማድረግ እንዲችሉ መሳርያዎች ይሰጣሉ፣ ከአከባቢ የሚመጣ ችግር በማስወገድ ሰዎች አከባቢያቸውን መላመድ እንዲችሉ ይረዳሉ
- አንዳንድ አገልግሎቶች በ Enhanced Primary Care Program በታች ሆነው በመዲኬር ይከፈላሉ። ይህን በተመለከተ የቤተሰብ ሓኪምዎን (GP) ይጠይቁ
- በሆስፒታሎች፣ በኮሚኒቲ የጤና ማእከሎች እና በግል ይሰራሉ
- የኦኩፐሽናል ቴራፒስቶች ማህበር በአውስትራልያ በዚህ ዌብሳይት ይመለከቱ www.ausot.com.au



## ኦፕቶመትሪ (Optometry)

- ኦፕቶመትሪስቶች የዓይን እና የማየት ምርመራ ያደርጋሉ፣ የዓይን መነጽር እንዲሁም ኮንታክት ሌንስ ያዝዛሉ፡ እንዲሁም ደግሞ ሌሎች የተለያዩ የዓይን በሽታዎች ያክማሉ
- ኦፕቶመትሪስቶች፡ የዓይን ቀዶ ጥገና አያደርጉም፡ ነገር ግን ዓይን የሚያክም መድሀኒት ሊያዙ ይችላሉ
- አብቻኞቹ ኦፕቶመትሪስቶች በግል የሚሰሩ ሲሆኑ በአብዛኞቹ የገበያ ማእከሎችና እንዲሁም በመኖርያ ቤቶች አከባቢ ይገኛሉ። መዲኬር በሕክምና ምክንያት ብዙ ጊዜ በዓይን ሐኪም መታየት ከሌለብዎት በስተቀር በየሁለት ዓመት የሚደረግ የዓይን ምርመራ ወጪ ይከፍላል፡
- የኩንስላንድ የጤና አገልግሎት፡ ለአንዳንድ የሚገባቸው ሰዎች ነጻ የSpectacle Supply Scheme ይሰጣል። ይህ አገልግሎት የሚገባዎት መሆኑን ለማወቅ ሐኪምዎን ይጠይቁ።
- የአውስትራልያ የኦፕቶመትሮች ማህበር www.optometrists.asn.au

ይህ መረጃ ጽሑፍ 10 ተከታታይ ክፍሎችን የያዘ ነው። በሙሉ ሲታይ፥


1፡ የጤና አጠባበቅ ዘዴ በኩንስላንድ
2፡ በሐኪም መታየት
3፡ መድሀኒቶች
4፡ የኩንስላንድ ሆስፒታሎች
5፡ የኮሚኒቲ የጤና ማእከላት
6፡ የጥርስ ሕክምና አገልግሎቶች
7፡ አላይድ (Allied) የጤና አገልግሎቶች
8፡ በጤንነት መኖር እና በሽታን መከላከል
9፡ ለተለዩ ብዱኖች የሚሰጥ የጤና እና የድጋፍ አገልግሎቶች
10፡ እርስዎ እና የጤና አገልግሎት ዘዴ ያካትታል።